አና ጓደኞቻቸ ኩብል ስቶን ንጣፍ ሀ/ሽ/ማህበር

AND FRINDS CABBLE STONE PAVING P/S

የመመስረቻ ጹሑፍ

አንቀጽ አንድ

ምሥረታ

በሰነዱ ግርጌ ፊርማቸውን ባሰፈሩት መካከል በኢትየጵያ ንግድ ሕግ በዚህ የመመስረቻ ጽሑፍና ተያይዞ በሚገኘው የመተዳደሪያ ደንብ ስምምነቶች የሚገዛና አላማ ው ከዚህ በታች በአንቀጽ 4 ሥር የተመለከቱትን የንግድ ሥራ ተግባራት ማከናወን የሆነ **አና ጓደኞቻቸ ኩብል ስቶን ንጣፍ ሀ/ሽ/ማህበር**

AND FRINDS CABBLE STONE PAVING P/S

/ለመመስረት ስምምነት ተደርጓል።

አንቀጽ ሁለት

የመስራች አባላት ስም፣ ዜግነትና አድራሻ

ተ.ቁ	የአባላት ስም	ዜግነት	አድራሻ			
			ከተማ	ክ/ከተማ	ወረዳ ቀበሌ	የቤ.ቁ
1		ኢትዮጵያዊ	አአ			
2		ኢትዮጵያዊ	አአ			
3		ኢትዮጵያዊ	አአ			
4		ኢትዮጵያዊት	አአ			
5		ኢትዮጵያዊት	አአ			
6		ኢትዮጵያዊ	አአ			

አንቀጽ ሦስት

የማህበሩ ስምና ዋና መሥሪያ ቤት

3.1 **የማህበሩ ስም .....አና ጓደኞቻቸ ኩብል ስቶን ንጣፍ ሀ/ሽ/ማህበር ..... AND FRINDS CABBLE STONE PAVING P/S** ነው።

3.2

አባላቱ ወደፊት በሌሎች የኢትዮጵያ ከተሞች ሆነ ከኢትዮጵያ ውጭ ቅርንጫፍ የመክፈት መብታቸው እንደተጠበቀ ሆኖ የተመዘገበው የማኅበሩ ዋና መ/ቤት በ አዲስ አበባ ከተማ ..... ክ/ከተማ ወረዳ ... የቤት ቁጥር ..... ውስጥ ነው።

አንቀጽ አራት

የማህበሩ የንግድ ሥራ ዓላማዎች

ማህበሩ የሚከተሉትን ዓላማዎች ይኖሩታል

1. በኩብል ስቶን ንጣፍ ስራ ላይ መሰማራት
2. ከእኛም አለፎ ለማህበረሰቡ የስራ እድል መፍጠር

አንቀጽ አምስት

የማህበሩ ካፒታልና የአክሲዮን ድልድል

5.1 የማኅበሩ ጠቅላላ ካፒታል w` **5000** /አምስት ሺህ ብር/ ሲሆን ይህም የማህበሩ ካፒታል ተጠቃሎ በጥሬ ገንዘብ ገቢ ተደርጓል።

5.2 የማህበሩ ካፒታል አንድ አክሲዮን ዋጋ ብር 1,000 (አንድ ሺህ ብር) ዋጋ ባላቸው በ 5000/አምስት ሺህ ብር አክሲዮኖች ተከፋፍሏል።

የአክሲዮን ድልድሉም በሚመለከተው መለኩ ተቀምጧል።

;.ا	ስም	የአክሲዮን መጠን	የአንዱ አክሲዮን ዋጋ በብር	የጠቅላላ ዋጋ በብር መዋጮ
1		**1**	**1000**	**1000**
2		**1**	**1000**	**1000**
3		**1**	**1000**	**1000**
4		**1**	**1000**	**1000**
5		**1**	**1000**	**1000**
	ጠቅላላ ድምር	**100**	**....**	**5000**

አንቀጽ ስድስት

የአባላቱ ኃላፊነት

አባላቱ ከላይ የተጠቀሰው ካፒታል ጥሬ ገንዘብ በሙሉ የተከፈለ መሆኑን በአንድነትና በነጠላ አረጋግጠዋል። ስለሆነም የአባላቱ ኃላፊነት በማህበሩ ውስጥ ባ ላቸው አክሲዮን መጠን የተወሰነ ነው።

አንቀጽ ሰባት

የትርፍና ኪሳራ ክፍፍል

አባላቱ በተለያየ ሁኔታ ካልተስማሙ በስተቀር ከጠቅላላው አመታዊ ትርፍ ሕጋዊ የመጠባበቂያ ገንዘብ እና ሌሎች ጠቅላላ ወጪዎች ከተቀነሱ በኋላ ቀሪው በአባላት መካከል እንደ አክሲዮን ይዞታቸው ይከፋፈላል። ኪሳራ ካለ በተመሳሳይ ሁኔታ በአባላቱ መካከል ይከፋፈላል። ሆኖም በማንኛውም ሁኔታ አባላቱ በማህበሩ ውስጥ ካለው የአክሲዮን ካፒታል በላይ እንደ አክሲዮን መጠናቸው ተጠያቂ ሊሆኑ ይችላሉ።

አንቀጽ ስምንት
ሥራ አመራር

የማኅበሩ ሥራ አስኪያጅ ሥልጣንና ተግባሩ በዚህ የመመስረቻ ጽሁፍ ሰነድ ላይ በዝርዝር የተመለከቱ ከአባላቱ መካከል ወይም ከውጭ በአባላቱ በሚመረጥ፣ የሥልጣን ዘመኑ ላልተወሰነ በሆነ አንድ ዋና ሥራ አስኪያጅ ይመራል። በዚህ ..... የመጀመሪያ የማኅበሩ ዋና ሥራ አስኪያጅ እንዲሁም የማህበሩ ምክትል ሥራ አስኪያጅ .....። ሆነው ተመርጠዋል።

የማኅበሩ ዋና ሥራ አስኪያጅ የሥራ ዘመናቸው ሲያልቅ በድጋሚ ሊመረጡም ይችላላሉ፤ ሆኖም የማህበሩ አባላት አስፈላጊ ሆኖ ባገኙት በማንኛውም ጊዜ ዋና ስራ አስኪያጁን የመሻር ስልጣን አላቸው። ማኅበሩ በዋና ሥራ አስኪያጅ እንደ አስፈላጊነቱ የሚሾሙ የዘርፍ ሥራ አስኪያጆች ሊኖሩት ይችላል። የሥራ አስኪያጅ ስልጣንና ተግባር የሚከተለው ይሆናል።

8.1 .የዘርፍ ሥራ አስኪያጅ ይሾማል፣ ይሽራል፣ ተግባራቸውን በዘርዝር ይሰጣል፣ ይቆጣጠራል።

8.2 ማኅበሩን በመወከል ይፈርማል።

8.3 ለማህበሩ የሚከፈል ገንዘብ መቀበል፣ የማኅበሩን ዕዳዎች መክፈል፣ ማናቸውም የሐዋላ ወረቀት የተስፋ ሰነድ፣ የባንክ ሰነድ ማዘጋጀትና በጀርባ ላይ መፈረም፣ ማደስና መክፈል እንዲሁ የቦንድ ሰርተፊኬቶችን ወይም ማናቸውንም ሰነዶች ማጽደቅና ከጀርባው መፈረም።

8.4 ለማኅበሩ ቴክኒካዊና አስተዳደራዊ ተግባሮች ኃላፊ ነው።

8.5 የማኅበሩ ወኪል ወይም ሠራተኛ ይቀጥራል፣ ያሰናብታል፣ ክፍያውን፣ ደሞዙን ጉርሻና ሌሎች ከመቀጠርና ከመሰናበት ጋር የተያያዙ ሁኔታዎችን ይወስናል።

8.6 ለማኅበሩ ንግድ በመልካም ሁኔታ መካሄድ የሚጠቅሙ ግዢዎች ሽያጭና የእነዚህን ማዘዣዎች ይወስናል።

8.7 ከማኅበሩ ንግድ ጋር የተያያዙ ማናቸውንም የንግድ ልውውጥ በተመለከተ ከሦስተኛ ወገኖች ጋር ውል ይዋዋላል።

8.8 በማናቸውም ፍርድ ቤት ማኅበሩ ከሳሽ፣ ተከሳሽ ወይም ጣልቃ ገቢ በሚሆንበት ጉዳይ ሁሉ ማኅበሩን በመወከል አስፈላጊውን ይፈጽማል። እንደዚሁም የሕግ ጠበቃ ወይም አማካሪ በመወከል ይከራከራል።

8.9 ማኅበርተኞች ሊቀበሉትና ሊያዩድቁት እንዲችሉ የሂሳብ ወጪና የገቢ መዝገብ በደንቡ እንዲያዝ አስፈላጊውን እርምጃ ይወስዳል። የማኅበሩ ዓላማ ግቡን እንዲመታ አስፈላጊ መስሎ በታየው ጊዜ ለዋና ሥራ አስኪያጅ ከተሰጡት ስልጣንና ተግባር መሀል ማንኛውንም በሌላ ለሦስተኛ ሰው እንዲፈጸም በማኅበሩ ስም ውክልና መስጠት ይችላል።

8.10 በማህበሩ ስም ቤት ያከራያል ይከራያል፣ የኪራይ ውል ይዋዋላል

8.11 የማህበሩ ስራ አስኪያጅ በድርጅቱ ስም አዲስ የባንክ ሂሳብ ይከፍታል ገንዘብ ገቢ ወጪ ያደርጋል፣ ቼክ ላይ ይፈርማል፣ቼክ ላይ ይፈርማል፤ቼክ ይቀበላል፣ ቼክ ይሰጣል፣ ቼክ ይመነዝራል

8.12 የማህበሩ ስራ አስኪያጅ በድርጅቱ ስም ተመዝግቦ የሚገኘውን የሚንቀሳቀስም ሆነ የማይንቀሳቀስ ንብረት ይሸጣል፣ይለውጣል፣ በዋስትና በማስያዝ ገንዘብ ከባንክም ሆነ ከአበዳሪ ድርጅቶች እንዲሁም ከግለሰብ ይበደራል፣ የብድር እና የመያዣ ውል ላይ ይፈርማል ።

8.13 የማህበሩ ስራ አስኪያጅ በድርጅቱ ስም የሚንቀሳቀስም ሆነ የማይንቀሳቀስ ንብረት ይገዛል ስሙን ወደ ድርጅቱ ስም ያዛውራል።

8.14 የማህበሩ ስራ አስኪያጅ ሌላ ሶስተኛ ወገን ለሚበደረው ብድር የማህበሩን የሚንቀሳቀስም ሆነ ማይንቀሳቀስ ንብረት በዋስትና ያስይዛል።

8.15 በማህበሩስምማንኛውንምአይነትየስራውልመዋዋልበማህበሩስምአክሲዮንመግዛትናበማህበሩስምቢሮመክራየትእንዲችሉ።

8.16 በማህበሩስምበማንኛውምመንግስታዊሆነመንግስታዊባልሆኑድርጅቶችመስሪያቤትበመቅረብጉዳዮችንበመከታተልእንዲያስፈጽሙ

8.17 የዋና መዝገባ ፣ የግብር ከፋይ ሰርተፊኬት፣ የቫት ሰርተፊኬት የብቃት ማረጋገጫ እንዲያወጡ እንዲያሳድሱ ዘርፍ መጨመር እንዲችሉ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ የንግድ ፈቃድ ተመላሽ ማድረግ እንዲችሉ

8.18 ግብርም ሆነ ማንኛውንም ለመንግስት የሚከፈሉ ክፍያዎችን እንዲከፍሉ ደረሰኝ እንዲቀበሉ ክሊራንስ እንዲጠይቁና እንዲቀበሉ።

8.19 በማህበሩስምማንኛውንምአይነትየስራውልመዋዋልበማህበሩስምአክሲዮንመግዛትና በማህበሩ ስም ቢሮ መክራየት እንዲችሉ።

8.20 የማህበሩ ዋና ስራ አስኪያጅ በሚኖሩበትም ሆነ በማይኖሩበት ጊዜ የማህበሩም/ስራ አስኪያጅ የማህበሩን ስራ አስኪያጅ ስልጣን እና ተግባር ሙሉ በሙሉ ተክተው ይሰራሉ /ያከናውናሉ/።

አንቀጽ ዘጠኝ
የማህበሩ ኦዲተር

ማህበሩ በአባላቱ የሚመረጡ ኦዲተር /ኦዲተሮች/ ይኖሩታል።

አንቀጽ አስር
አክስዮኖች ስለማስተላለፍ

1. አክሲዮን በማህበርተኞች መካከል የለገደብ ይተላለፋል።
2. ማህበርተኛው የአክሲዮን ግዢ የቅድሚያ መብት አለው።
3. ከባለ አክሲዮኖች የካፒታል 75% የያዙ ካልተስማሙ በስተቀር አክሲዮኖች ለሌላ ሶስተኛ ወገኖች አይተላለፍም።
   የአባላቱ ስምምነት ካልተገኘና አክስዮን ማስተላለፍ የፈለገው አባል በሀሳብ ከፀና ለሽያጭ የቀረበው አክስዮን ለመግዛት ቅድያ የሚሰጠው ለአባላቱ ሆኖ ከመካከላቸው በጨረታ አሸናፊ ለሚሆነው አባል ይሸጣል።
4. የአክስዮኖች ዋጋ በጋራ በሚደረግ ስምምነት ይወሰናል።

አንቀጽ አስራ አንድ

አክሲዮን ማስተላለፍ መርህ

1. አክሲዮን ለማስተላለፍ የሚፈልግ ማህበርተኛ የአክስዮን ድርሻውን የማንነቱን ሙሉ መግለጫ በያዘ ደብዳቤ ለሥራ አስኪያጅ ያሳውቃል።
2. በሕግ አግባብና በዚህ ደንብ የተደነገገው ሥርዓት ሲሟላ አክስዮን ወደ 3ኛ ወገን ሊተላለፍ ይችላል።
3. ሥራ አስኪያጁ ደብዳቤ በደረሰው በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ስለ አክሲዮን መተላለፍ ለማህበርተኞች በጽሑፍ ያሳውቃል።
4. ድርሻን ለወራሾች በማስተላለፍ ረገድ ይህ አንቀጽ ተፈጻሚነት ይኖረዋል፣ወራሾች ሌላ ማህበርተኛ የሚኖረው መብትና ግዴታ አላቸው።

አንቀጽ አስራ ሁለት

የማህበሩ አባላት መብትና ግዴታዎች

4.1 እያንዳደንዱ አባል የሚከተሉት መብቶች ይኖሩታል ፤

ሀ. በማናቸውም የአባላት ስብሰባ ላይ የመካፈል ፤

ለ.በማናቸውም ስብሰባ ላይ በያዘው የአክሲዮች ብዛት መጠን ድምፅ የመስጠት ፤

ሐ. በዋናው መስሪያ ቤት ውስጥ ያለ የቆጠራ ውጤቶች የወጪና ገቢ ምዝገባዎና የኦዲተር ሪፖርቶች የመመርመርና መዝግቦ የመያዝ ፤

መ. በሕግ በማህበሩ መመስረቻ ጽሁፍ የተመለከቱትን መብቶች መጠቀም አለበት ።

4.2 ከላይ የተመለከተው የአባላት መብት እንደተጠበቀ ሆኖ

ሀ

.ማህበሩ ለአንድ አክሲዮን ከአንድ በላይ ባለ ንብረት አይቀበልም። ስለሆነም በዚህ መሰረት የአክሲዮን የጋራ ባለንብረቶች ቢኖሩ የአባላነት መብ ታቸውን ሊጠቀሙበት የሚችሉ ከመካከላቸው አንድ እንደራሴ በመሾም ብቻ ነው።

ለ .

ከአክስዮኖች ጋር የተያያዙ መብቶች አክስዮኑን ይከታተላሉ ። የአክስዮን ባለቤት የሆነ የተፈጥሮ ሰውም ሆነ በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው በደ ንቡ መሰረት በመብቶቹ ሊገለገል ይችላል ። በአንዳንዱም የአክሲዮን ባለቤት መሆን ለዚህ መመመሰረቻ ፅሁፍና በአግባቡ ለሚተላለፉ የአባላት ውሳኔ ዎች ተገዢ የመሆን ውጤቶች ያስከትላል ።

ሐ .

የሚች ማህበርተኞች ወራሾችም ሆኑ ወኪሎች በማህበሩ ንብረቶች ላይ ማህተም እንዲደረግ ወይም እንዲታሸግ የማድረግ መብት አይኖራቸውም ። ስለሆነም በመብታቸው በሚጠቀሙበት ጊዜ ሁሉ የመመስረቻ ጽሁፍ የመተዳደሪያ ደንብና በአግባቡ የሚተላለፉ የማህበርተኞች ውሳኔዎች ሁሉ በ እነርሱም ላይ ተፈፃሚነት አላቸው ።

አንቀት አስራ ሦስት

ሰነዶችን የማወቅ መብት

ማናቸውም ባለአክስዮን ከማህበሩ ዋና መሥሪያ ቤት ከዚህ ቀጥሎ ያሉትን ሰነዶች ለማወቅ ወይም ቅጂዎቻቸውን ለመውሰድ በማናቸውም ጊዜ ሁሉ መ ብት አለው።

እነዚህም፡-

ሀ/ የሂሳብ ሚዛኖች፣ የትርፍና የኪሳራ ሂሳቦች

ለ/ አስተዳዳሪዎቹና ተቆጣጣሪዎች ባለፉት የመጨረሻ ሦስት (3) የሂሳብ ማጠቃለያ ጊዜዎች ስለሥራው ባለአክሲዮኖች ያቀረቡዋቸው ሪፖርቶች

ሐ/የገባኤ ቬርሻሎችና ሌሎች የማስረጃ ወረቀቶች ናቸው።

አንቀጽ አስራ አራት

የዋና ስራ አስኪያጅ ክፍያ

የዋና ሥራ አስኪያጅ ደመወዝ፣አበልና ሌሎች ጥቅሞች በማህበርተኞች 75% የያዙ የአክስዮን አባላቶች የሚወሰን ይሆናል።

አንቀጽ አስራ አምስት

ስብሰባዎችን ስለመጥራትና የወሳኔ አሰጣጥ

ምልዐተ ጉባኤ

የማህበሩ ስብሰባ ሊካሄድ የሚችለው ከጠቅላላ ባለ አክስዮኖች ከግማሽ በላይ ድምጽ የሚወክሉ ማህበርተኞች ወይም ህጋዊ ወኪሎቻቸው በስብሰባው ላ ይ ሲገኙ ነው፣ በዚህ አይነት ስብሰባዎች ላይ ወሳኔዎች የሚተላለፉት ማህበሩ ውስጥ ባላቸው የአክስዮን ድርሻ ልክ በድምጽ ብልጫ ይሆናል።

15.1 **ማህበሩ የበጀት ዓመቱ ሲያልቅ መደበኛ ስብሰባ ያካሂዳል። የማህበሩ የሂሳብ አመት ከተዘጋጀበት አራት ወር ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ የማህበሩ ጠቅላ ላ ጉባኤ መጠራት አለበት፤ዋናው ስራ አስኪያጁ አመታዊ የማህበርተኞች ስብሰባ ከመደረጉ በፊት 15 ቀን ባላነሰ ጊዜ አስቀድ ለአባላት በአደራ ደብዳቤ የስብሰባውን ጥሪ ማሳወቅና ለውሳኔው ወይም ለውይይት ያቀረበው ሀሳብ ምን እንደሆነ በግልጽ ማስረዳት አለበት።**

15.2 **ለማህሩ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ዋና ሥራ አስኪያጅ በማናቸውም ጊዜ ስብሰባ ሊጠራ ወይም አባሎችን በተናጠል ሊያነጋግር ይችላል እንዲሁም አዲተሩ ወይም ደግሞ 75% በላይ የአክስዮን ድርሻ ያላቸው የማህበሩ አባላት በማንኛውም ጊዜ የማህበሩ ጠቅላላ ጉባኤ እንዲሰበሰብ ሊያደርግ ይችላል።**

15.3 **ማህበሩ ስብሰባ በንግድ ህግ ቁጥር በተደነገገው መሠረት የማህበርተኞች ስብሰባ ሊጠራ ይችላል።**

15.4 **የማህበሩ መመስረቻ ጹሁፍና መተዳደሪያ ደንቡን ለማሻሻል፣ማህበሩ እንዲፈርስ ለመጠየቅ፣የማህበሩን ዕድሜ ለመወሰን ከሌላ ማህበር ጋር በመቀላቀል ለማደራጀት፣የማህበሩን ተፈጥሮ ለመለወጥ፣ካፒታ ለመቀነስ ወይም ለመጨመር፣አዲስ አባላትን ለመቀበል ድርሻን ለውጪ ሰዎች ለማ ስተላለፍ 75 የአክስዮን ባለድርሻዎች ምልዐተ ጉባኤ ይሆናል።**

15.5 ሌሎች ጉዳዮች በንግድ ህግ ቁጥር መሠረት ይወሰናሉ።

አንቀጽ አስራ ስድስት
የሂሳብ ዓመትና የትርፍ ክፍፍል

16.1 የማህበሩ የሂሳብ ማጠቃለያ ጊዜ በየአመቱ ከሐምሌ 1 ቀን እስከ 30
ድርስ ይሆናል። ሆኖም የመጀመሪያ ጊዜ ማህበሩ ከተመዘገበበት ጀምሮ እስከ ሰኔ 30 ይሆናል።
16.2 የማህበሩ ቆጠራ የሂሳብ ማመዛዘኛ የዓመቱ ትርፍና ኪሳራ ሰንጠረዥ (ሪፖርት)በዋና ሥራ አስኪያጅ ይዘጋጃል።
16.3
ከዓመቱ የተጣራ ትርፍ በማህበርተኞች የሚወሰን የመጠባበቂያ ተቀማጭና ሌሎች ወጪዎች ተቀናንሶ የሚገኘውን የተጣራ ትርፍ ለማህበረተኞች እ
ንደአሰራሮን ድርሻቸው ይከፋፈላል።
16.4 በንግድ ሕጉ አንቀጽ 539 እንደተደነገገው በተጣራው ትርፍ ላይ በየአመቱ መጠባበቂያ ቢያንስ 5
በመቶ እየተነሳ ይቀመጣል። ይኽውም መጠባበቂያ ከማህበሩ ዋና ካፒታል አንድ አስረኛ እጅ ሲደረስ ግዴታ መሆኑ ይቋረጣል።

አንቀጽ አስራ ሰባት
የጠቅለለ ጉባኤ ስልጣንና ተግባር

17.1 የማኅበሩን ዋና ስራ አስኪያጅ መግለጫ ሰምቶ ተቀባይነት ያለው ሆኖ ካገኘው ያፀድቃል።
17.2 የማህበሩን ሂሣብ ተቆጣጣሪ /ኦዲተር/ዓመታዊ መገልጫ መርምሮ ተገቢውን እርምጃ ይወስዳል።
17.3 የማህበሩን ዋና ሥራ አስኪያጅ ይሾማል በቂ ምክንያት ሲኖር በንግድ ሕግ ቁጥር በተደነገገው መሠረት ይሽራል።
17.4 የማህበሩን የሥራ አፈፃፀም በሚመለከት ለዋናው ሥራ አስኪያጅ መመሪያ ይሰጣል።
17.5 የማኅበሩን ማስፋፋት ወይም ማፍረስ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ውሳኔ ይሰጣል።

አንቀጽ አስራ ስምንት
ኦዲተር

18.1 በማህበርተኞች የሚመረጥ የተረጋገጠለት የኦዲት ባለሙያ ግለሰብ ወይም ድርጅት ይኖረዋል።
18.2 የአገልግሎት ክፍያው በማህበርተኞ ይወሰናል።
18.3 የማህበሩን ሂሳብ በመመርመር ለአባላት ወይም ለጠቅላላ ስብሰባ ሪፖርት ያቀርባል።
18.4 በዋና ሥራ አስኪያጅ ዓመታዊ ሪፖርት ሙያዊ አስተያየት ይሰጣል።
18.5 ማንኛውም የማህበሩ ሰነዶች ይመረምራል።
18.6 ከሚመለከታቸው ማህበርተኞች ማብራሪያ የመጠየቅና የማግኘት መብት አለው።
አስፈላጊ ሆኖ ባገኘው ጊዜ በማበርተኞች ስብሰባ የመገኘት መብት ይኖረዋል።

አንቀጽ አስራ ዘጠኝ
የማህበሩ መፍረስ

19.1 በማህበርተኞች ችሎታ ማጣት፣መክሰር፣እዳውን መክፍለ ካልቻለ ወይም በሞት ማህበሩ አይፈርስም።
19.2 ማህበሩ በሚፈርስበት ጊዜ በማህበርተኞች የተሰየመ ሶስተኛ ወገን ሒሳብ አጣሪ ይሆናል።
19.3 ሒሳብ አጣሪው የተመረጠበትን በመወጣት ረገድ ሙሉ ስልጣን አለው።
19.4 ቋሚ ንብረት ዕዳውን አጣርቶና ለይቶ በማወቅ የማህበሩን ዕዳ ለመጠያቂዎች ያከፋፍላል።
19.5 ዕዳ ተከፍሎ የሚቀር ትርፍ ለማህበርተኞች እንደየድሻቸው ያከፋፍላል።
19.6 ማኅበሩ በንግድ ሕግ ቁጥር መሠረት በቂ በሆኑ ምክንያቶች በፍርድ ቤት ወሳኔ ይፈርሳል።

አንቀጽ ሃያ
መመስረቻውን ስለማሻሻል

አግባብ ባለቸው የንግድ ህግ ድንጋጌዎች መሠረት ማህበርተኞች ይህን የመመስረቻ ጹሑፍ አስፈላጊ በሚሆንበት ጊዜ ሁሉ ለመለወጥ ለማሻሻልና ተ
ጨማሪ ሃሳቦችንም ለማከል ይችላል።

አንቀጽ ሃያ አንድ
ውዝግብን ስለመፍታት

በማህበርተኞች መካከል የሚነሱ ማህበር ነክ አለመግባባቶች በኢትዮጵያ ፍትሐብሔር ህግና የሥነ ሥርዓት ሕግ ስለግልግል በተመለከቱት ደንቦች
መሠረት ይወሰናል ውሳኔው አስገዳጅና የመጨረሻ ነው።

አንቀጽ ሃያ ሁለት
መመስረቻ ጹሁፉ በሥራ ላይ የሚውልበት ጊዜ

ይህ የመመስረቻ ጹሁፍ በህግ አግባብ ከጸደቀበት ጊዜ ጀመሮ በሥራ ላይ ይውላል።

አንቀጽ ሃያ ሦስት
ማህበሩ የሚቆይበት ጊዜ

አባላቱ በተለየ ሁኔታ ለመወሰን ያለው መብት እንደተጠበቀ ሆኖ ማኅበሩ ላልተወሰነ ጊዜ ተቋቁሟል።
ከዚህ በላይ በዝርዝር በሰፈሩት ጉዳዮች ላይ መስማማታቸንን ይታወቅ ዘንድ እኛ ማህበርተኞች ፊርማችንን አኑረናል።

አንቀጽ ሃያ አራት
የማህበሩ የሥራ ዘመን

አባላቱ በተለየ ሁኔታ ለመወሰን ያላቸው መብት እንደተጠበቀ ሆኖ ማኅበሩ የተቋቋመው ላልተወሰነ ጊዜ ነው።

ይህ የመመስረቻ ፅኑፍ ዛሬ ታህሳስ 26 ቀን 2017 ዓ.ም በመስራች አባላትና ፈራሚዎች በአዲስ አበባ ከተማ ተመስረተ።

ተ.ቁ	ስም	ፊርማ
1		
2		
3		
4		
5		
6		